# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት


**የሰ/መ/ቁ.** 234443

ጥር 24 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሰናይት አድነው

**አመልካች-** አቶ ሲሳይ ሀይሉ - ቀርበዋል

**ተጠሪ-** አቶ ተስፋዬ ተ/መድን - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረዉ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ አመልካች መስከረም 15 ቀን 2013 ዓ.ም ለወሰደዉ የስድስት በሬዎች ዋጋ ብር 174000.00 ለክፍያ ቼክ የሰጠዉ ቢሆንም ቼኩ ስንቅ እንደሌለዉ መረጋገጡን ተከትሎ ገንዘቡን እንዲከፍለዉ ጠይቆት አመልካች ፍቃደኛ አለመሆኑን ጠቅሶ ገንዘቡን ጥቅምት 15 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር አመልካች እንዲከፍለዉ የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

አመልካች በሰጠዉ መልስ ቼኩ ለተጠሪ የተሰጠዉ ለመተማመኛ መሆኑን፣ ቼኩ ከተሰጠ በኋላ አመልካች ከሚጠበቅበት ክፍያ ዉስጥ በባንክ እንዲሁም በእጅ በተለያዩ ጊዜያት ብር 138,000.00 ለተጠሪ ከፍሎ ቀሪዉ ብር 36,000.00 ብቻ ሆኖ እያለ ቼኩ በእጁ ስላለ ብቻ እንዳልተከፈለዉ አድርጎ ተጠሪ ያቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የልዩ ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ቼክ ላይ የተመለከተዉን ብር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

174,000.00 በተለያዩ ጊዜያት ለተጠሪ በእጁ እና በባንክ በኩል የከፈለ መሆኑን በአመልካች ማስረጃዎች ከተጠሪ ማስረጃዎች በተሻለ ሁኔታ የተረጋገጠ መሆኑን ጠቅሶ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ በስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን ማስረጃዎች እንደገና መዝኖ አመልካች ከተጠሪ ለወሰዳቸዉ የእርድ በሬዎች ክፍያ ብር የሚሆን ብር 174,000.00 ቼክ ወስዶ ነገር ግን ቼኩ ስንቅ የሌላዉ መሆኑ እና አመልካች ክፍያዉን ለተጠሪ ስለመፈጸሙ አለመረጋገጡን፣ ነገር ግን ብር 40,000.00 ክፍያ የተከፈለዉ መሆኑን ተጠሪ ክዶ አለመከራከሩን ጠቅሶ ከብር 174,000.00 ዉስጥ 40,000.00 ተቀንሶ ብር 134,000.00 ከጥቅምት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9%፣ ለጠበቃ 10% ብር 13,400.00፣ የዳኝነት በተወሰነዉ የሚታሰብ ብር 3,860.00 ከወጪና ኪሳራ 3,000.00 ብር ጋር ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች መስከረም 09 ቀን 2015 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ የሰበር አቤቱታ አመልካች በእራሴ እና በባለቤቴ ስም በአጠቃላይ ብር 138,000.00 ለተጠሪ መክፈሌን ምስክሮች አረጋግጠዉ እያለ የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረቡት የአመልካች ምስክሮች ተአማኒነት የላቸዉም በሚል ዉድቅ በማድረግ በሌላ በኩል የተጠሪ ምስክሮች ልጆቹ ሆነዉ ሳለ እንደ ተአማኒ ማስረጃ ተቀብሎ መወሰኑ እርስ በእርሱ የሚጣረስ እና የእኩልነት መርህን የጣሰ ነዉ፡፡ ቼኩን በጥበብ ሀይሉ ስም ፈርሜ መስጠቴ እራሱ ለዋስትና የተሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሲሆን፣ ክፍያዉም ለተጠሪ የተፈጸመ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ቼኩን እንደ ክፍያ ሰነድነት ቆጥሮ የደረሰበት ድምዳሜ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነዉ በማለት ታርሞ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሰጠዉን ዉሳኔ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የሻረበትን አግባብ ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ ግንቦት 16 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማስረጃን መዝኖ የሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ጠቅሶ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ዉድቅ እንዲሆን ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሰኔ 13 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፤

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ በጸናዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደቻለዉ ተጠሪ ላቀረበዉ የብር 174,000.00 ክፍያ ጥያቄ መሠረት ያደረገዉ አመልካች የስድስት በሬዎችን ዋጋ በቼክ ሰጥቶት ቼኩ ስንቅ የሌለዉ በመሆኑ ያልተከፈለዉ መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን፣ አመልካች በበኩሉ በተለያዩ ጊዜያት ብር 138,000.00 ለተጠሪ ከፍሎ ቀሪ ብር 36,000.00 ብቻ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ በዚህ ክርክር መነሻነት ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኝን ምስክሮች መርምሮ አመልካች ክፍያዎቹን መፈጸሙ ተረጋግጧል በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የተጠሪን ክስ ዉድቅ ያደረገ ቢሆንም፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን ምስክሮች ቃል እንደገና በመመርመር ከብር 40,000.00 ዉጪ ቀሪዎቹን ክፍያዎች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች ለተጠሪ ስለመክፈሉ አልተረጋገጠም በሚል የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ይህ ድምዳሜ ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን ባለዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በተመለከተዉ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ሲደርስ የፈጸመዉ የማስረጃ አቀባበል እና የምዘና መርህ ስህተት ስለመኖሩ የዉሳኔዉ ግልባጭ አያሳይም፡፡

በሌላ በኩል በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በቀረበለት ይግባኝ መነሻነት የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ረገድ የደረሰበትን ድምዳሜ እንደገና በመመርመር እና የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመዘን የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንኑ በመቀበል በሰጠዉ ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 383524 ላይ መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 37164 ላይ ጥቅምት 15 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የሰበር አጣሪ ችሎት መስከረም 10 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**መ/ዐ**

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !